# የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) መተዳደሪያ ደንብ

**(በብልፅግና ፓርቲ የመጀመሪያ ጉባኤ የፀደቀ)**

**የካቲት 2014 ዓ.ም**
**ብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና)**
**አዲስ አበባ**

# ማውጫ

**ገፅ**


መግቢያ ........................................ 1

**ምዕራፍ አንድ** ........................................ 2

I. ጠቅላላ ድንጋጌዎች ........................................ 2

አንቀፅ አንድ - አጭር ርዕስ ........................................ 2

አንቀፅ ሁለት - የፓርቲው መጠሪያ ........................................ 2

አንቀፅ ሶስት - የፓርቲው አርማ ........................................ 2

አንቀፅ አራት - የፓርቲው የስራ ቋንቋዎች፣ ........................................ 3

አንቀፅ አምስት - የፓርቲው ልሳን፣ ........................................ 3

አንቀፅ ስድስት - የፓርቲው ፅህፈት ቤት ........................................ 3

አንቀፅ ሰባት - የፓርቲው ዓላማዎች፣ መርሆዎች፣ እሴቶችና የአሰራር ስርዓቶች ........................................ 4

አንቀፅ ስምንት - የፓርቲው ምርጫ መርህና የአሰራር ስርዓት ........................................ 7

**ምዕራፍ ሁለት** ........................................ 8

II. አባልነት ........................................ 8

አንቀፅ ዘጠኝ - የፓርቲው አባል ስለመሆን ........................................ 8

አንቀፅ አስር - ለአባልነት የሚቀርብ ጥያቄ ........................................ 8

አንቀፅ አስራ አንድ - የአባል መብት ........................................ 9

አንቀፅ አስራ ሁለት - የአባልነት ግዴታ ........................................ 10

አንቀፅ አስራ ሶስት - በአባላት ላይ በዲስፒሊን ጉድለት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች ........................................ 11

**ምዕራፍ ሶስት** ........................................ 12

III. የፓርቲው አወቃቀርና አደረጃጀት ........................................ 12

አንቀፅ አስራ አራት - የፓርቲ አወቃቀርና የአመራር አካላት ........................................ 12

አንቀፅ አስራ አምስት - የፓርቲው ጉባዔ፣ የክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ፣ የዞን፣ የከተማ፣ የወረዳና የቀበሌ የኮንፈረንሶች አወቃቀር ........................................ 13

አንቀፅ አስራ ስድስት - የፓርቲው ጉባዔ ........................................ 13

አንቀፅ አስራ ሰባት - የፓርቲው ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት፣ ........................................ 14

አንቀፅ አስራ ስምንት - የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ፣ ........................................ 15

አንቀፅ አስራ ዘጠኝ - የፓርቲው ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፤- 16
አንቀፅ ሃያ - የፓርቲው ፕሬዝዳንት 18
አንቀፅ ሃያ አንድ - የፓርቲው ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት 18
አንቀፅ ሃያ ሁለት - የፓርቲው የኢንስፔክሽንና ስነ-ምግባር ኮሚሽን 19
አንቀፅ ሃያ ሶስት - የፓርቲው ዋና ፅ/ቤት 21
**ምዕራፍ አራት 23**

IV. የፓርቲው የክልል አደረጃጀት 23
አንቀፅ ሃያ አራት - የፓርቲ አደረጃጀትና አወቃቀር 23
አንቀፅ ሃያ አምስት - የክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ፓርቲ ኮንፈረንስ የአሰራር ስርዓት፣ 24
አንቀፅ ሃያ ስድስት - የፓርቲ ኮንፈረንስ ተግባርና ኃላፊነት 24
አንቀፅ ሃያ ሰባት - የፓርቲ ክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ /አካባቢ አመራር ኮሚቴ 25
አንቀፅ ሃያ ስምንት - የፓርቲ ፅህፈት ቤቶች 26
አንቀፅ ሃያ ዘጠኝ - የብልፅግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ 26
አንቀፅ ሰላሳ - የብልፅግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ 27
**ምዕራፍ አምስት 28**

V. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች 28
አንቀፅ ሰላሳ አንድ - የስልጣን ዘመን 28
አንቀፅ ሰላሳ ሁለት - የፓርቲው የፋይናንስ ምንጮች 28
አንቀፅ ሰላሳ ሶስት - የፓርቲው የሰው ሀብት፣ ንብረት፣ ፋይናንስና የሂሳብ መዛግብት የአሰራር ስርዓት 28
አንቀፅ ሰላሳ አራት - በፓርቲው ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች አፈታት ስርዓት 29
አንቀፅ ሰላሳ አምስት - የፓርቲው ውህደት፤ ቅንጅት፤ ወይም ግንባር የመፍጠር ስርዓት 29
አንቀፅ ሰላሳ ስድስት - የፓርቲው መፍረስ 29
አንቀፅ ሰላሳ ሰባት - የፓርቲው አማካሪ የመማክርት ጉባኤ 29
አንቀፅ ሰላሳ ስምንት - የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ የበላይነት፣ 30
አንቀፅ ሰላሳ ዘጠኝ - መመሪያ የማውጣት ስልጣን 30
አንቀፅ አርባ - መተዳደሪያ ደንቡን ስለማሻሻል፣ መቀየር እና ስለመሻር 30
አንቀፅ አርባ አንድ - መተዳደሪያ ደንቡ ስለሚፀናበት ሁኔታ 31

## መግቢያ

እኛ የብልፅግና ፓርቲ አባላት የሃገራችን ኢትዮጵያን እድገትና የጋራ ብልፅግና እውን ለማድረግ በመነሳት፣

አገራችንን ወደሚቀጥለው ምዕራፍ ለማሻገር አዲስ ራእይና አዲስ ትርክት እንደሚያስፈልግ በማመን፣

የሕግ የበላይነትና ዴሞክራሲ የሰፈነባት፤ የግለሰብና ቡድን መብቶች በሚዛኑ የሚከበሩባት፤ ዜጎች ከድህነት ተላቀው በብልፅግና የሚኖሩባት፤ ጠንካራና ቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚታይባት፤ በአህጉራዊ፣ ቀጠናዊና ዓለም አቀፋዊው መድረክ ላይ ጉልህ ሚና የምትጫወት ኢትዮጵያን ለማየት ባለን ተስፋ፣

የበለፀገች፣ ሕብረ-ብሔራዊ ማንነቷ የዳበረና አንድነቷ የተጠናከረ ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ ባለን ቁርጠኝነት፣

ይህንንም ለመተግበር በመደመር አስተሳሰብና በአንድነት ቅኝት በመነሳት፣ ልናያት የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ ለመገንባት የእያንዳንዳችንን ርብርብ የሚጠይቅ መሆኑን በመረዳት፣ የበኩላችንን ሚና ለመጫወት በከፍተኛ ቆራጥነት ተሰባስበን መታገል በማስፈለጉ፣

የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) የሚመራበት የመተዳደሪያ ደንብ መቅረፅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ-ምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2011 የተደነገጉትን ህጎች የሚያከብር የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) ሰነድን በመስራች ጉባዔያችን መክረንበት ህጋዊ የፓርቲውን ሰነድ አድርገን አፅድቀናል።

# ምዕራፍ አንድ

## I. ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ አንድ - አጭር ርዕስ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ "የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና) መተዳደሪያ ደንብ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### አንቀፅ ሁለት - የፓርቲው መጠሪያ

የፓርቲው መጠሪያ "የብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና)" ነው።

### አንቀፅ ሶስት - የፓርቲው አርማ

1. **የአርማው ቀለምና አቀማመጥ**
   - በክብ ነጭ መደብ ውስጥ በስተግርጌ ጥቁር ቀለም ያላቸው ለማቀፍ የተዘጋጁ ሁለት የሰው እጅ ምስሎች ያሉት ሲሆን፣መሀል ላይ ለማቀፍ የተዘጋጁ የሰው እጅ ምስሉ ውስጥ ሆነው የሚታዩ ሶስት የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ሶስት ሰዎች የሚገኙበት ነው።ከዚህ በተጨማሪ ከውስጥ ወደ ውጭ የሚፈነጥቁ ቢጫ ቀለም ያላቸው የብርሃን ፍንጣቂዎችን በውስጡ አካቶ ያያዘ ነው።
2. **ጥቅል ትርጉም**
   - ዓርማው የሀገራችንን ህብረ ብሄራዊነትን፣ ሀገራዊ አንድነትን፣ ብሄራዊ ኩራት፣ ሰላምን፣ ዴሞክራሲንና የብልፅግናን አስተሳሰብ የያዘ ሆኖ ከውስጥ ወደ ውጭ እየሰፋ የሚሄድ የቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ትስስሮችን የሚያመላክት ነው።
3. **ዝርዝር ትርጉም**
   - እጅ፡-

     በሎጎው በስተግርጌ በኩል የተቀመጠው የሰው የእጅ ምስል ብልፅግና ሁሉን አቃፊ መሆኑን የሚወክል ሲሆን ቀለሙ ጥቁር የሆነበት ምክንያት ኢትዮጵያዊያን የጥቁር ህዝቦች የነፃነትና የድል ተምሳሌት መሆናችንን የሚወክል ነው።
   - **የሰዎች ምስል፡-**

     ብልፅግና ሰው ተኮር ፓርቲ መሆኑን የሚወክል ሲሆን ፓርቲው ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ ብልፅግና የሚታገል መሆኑን ይወክላል። የሰዎቹ ምስል ቀለማቸው

የተለያየ መሆኑ የኢትዮጵያን ብዝሃነት እንዲያሳይና ብዝሃነታችን የውበታችንና የጠንካራ አንድነታችን ምልክት ሆኖ ተወክሏል።

- **ጎህ፡-**

  ከላይ የተቀመጡት የብርሃን ፍንጣቂዎች ጎህን የሚወክሉ ሲሆን ጎህ ጨለማን ሰንጥቆ የሚመጣ ብርሃን እንደመሆኑ መጠን ብልፅግና ኢትዮጵያን ወደ ከፍታና የብርሃን ዘመን ለማሸጋገር የሚታገል ፓርቲ መሆኑን የሚወክል ነው። (የተስፋና የብልፅግና ዘመንን ይወክላል)

## አንቀፅ አራት - የፓርቲው የስራ ቋንቋዎች፣

1. ፓርቲው ለሁሉም የአገራችን ቋንቋዎች ሙሉ እውቅና ይሰጣል፤
2. በፌዴራል ደረጃ የፓርቲው የስራ ቋንቋ የሀገሪቱ ህገ-መንግስት እና ክልሎች በህገ-መንግስታቸው የስራ ቋንቋ አድርገው ያፀደቋቸው ቋንቋዎች ይሆናሉ።
3. የፓርቲው የየደረጃው ፅ/ቤቶች የየራሳቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ ቢያንስ አንድ የፓርቲውን የስራ ቋንቋ በተጨማሪነት መጠቀም ይችላሉ።

## አንቀፅ አምስት - የፓርቲው ልሳን፣

1. የፓርቲው ልሳን "**ብልፅግና**" ነው።
2. የፓርቲው ልሳን በፓርቲው የስራ ቋንቋዎች የሚዘጋጅ ብዝሃ ልሳን ነው።
3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) እንደተጠበቀ ሆኖ በሌሎች የሀገሪቱ እና የውጭ ቋንቋዎች ሊዘጋጅ ይችላል።

## አንቀፅ ስድስት - የፓርቲው ፅህፈት ቤት

1. የፓርቲው ዋና ፅህፈት ቤት አዲስ አበባ/ፊንፊኔ ይሆናል፣
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፓርቲው በክልል፣ በአዲስ አበባ ከተማና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በከተማ አስተዳደር /በዞን/ በልዩ ወረዳ/በዞን ደረጃ ያሉ ክፍለ ከተሞች፤ በወረዳ/በወረዳ ደረጃ ያሉ ከተሞች/በወረዳ ደረጃ ያሉ ክፍለ ከተሞች/ቀበሌዎች እና በቀበሌ ፅህፈት ቤቶች ይኖሩታል፣
3. እንደአስፈላጊነት በውጭ ሀገር ፅህፈት ቤቶች ሊያቋቁም ይችላል።

## አንቀፅ ሰባት - የፓርቲው ዓላማዎች፣ መርሆዎች፣ እሴቶችና የአሰራር ስርዓቶች

1. **የፓርቲው አላማዎች የሚከተሉት ናቸው**

   ሀ) ጠንካራ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ቅቡልነት ያለው፣ ዘላቂ ሀገረ-መንግስት መገንባት፤

   ለ) ልማትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አካታች የኢኮኖሚ ስርዓት መገንባት፤

   ሐ) ሁለንተናዊ ብልፅግናን የሚያሰፍን ማህበራዊ ልማትን ማረጋገጥ፣

   መ) ሀገራዊ ክብርንና ጥቅምን ማዕከል ያደረገ የውጭ ግንኙነት ማካሄድ፤

2. **የፓርቲው መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው፤**

   ሀ) ህዝባዊነት፤

   ለ) ዴሞክራሲያዊነት፤

   ሐ) የህግ የበላይነት፤

   መ) ልማትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት፤

   ሰ) ተግባራዊ እውነታ፤

   ረ) ሀገራዊ አንድነትና ህብረ-ብሔራዊነት፤

3. **የፓርቲው እሴቶች የሚከተሉት ናቸው፤**

   ሀ) የዜጎችና የህዝቦች ክብር፣

   ለ) ፍትህ፤

   ሐ) ህብረ ብሄራዊ ወንድማማችነትና እህትማማችነት፤

   ሰ) መከባበርና መቻቻል፤

   ረ) ህብረ-ብሔራዊ አንድነት፤

4. **የፓርቲው የአሰራር መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው፤**

   ሀ) ፓርቲው የሀገሪቱን እና የክልሎችን ሕገ-መንግስት እና ሌሎች ሕጎችን በማክበር ተግባራቱን ያከናውናል፣

   ለ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እስከ (3) የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የፓርቲው አባላት የመፈፀም፣ የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው፣

   ሐ) አባላት የግል ሃሳባቸውን የማራመድ መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርቲውን ውሳኔ የመፈፀምና የማስፈፀም ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፣

መ) ማንኛውም አባል በፓርቲ ውስጥ እኩል ድምፅና በውሳኔ ሂደቶች ውስጥ አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል፣

ሰ) የፓርቲ ውሳኔ በየደረጃው ዴሞክራሲያዊ ውይይት ከተካሄደበት እና የጋራ ግንዛቤ ከተያዘበት በኋላ በተባበረ ድምፅ እንዲወሰን ጥረት ይደረጋል፣

ረ) በተባበረ ድምፅ ለመፅደቅ ባልቻሉ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚተላለፈው በአብላጫ ድምፅ ይሆናል። ተፈፃሚነቱም በወሰነው አካል እና በታችኛው መዋቅር ላይ ይሆናል፣

ሰ) በሌላ አኳኋን በዚህ ደንብ ካልተደነገገ በስተቀር የፓርቲው ውሳኔ የሚያልፈው በአብላጫ ድምፅ ነው። የተሰጠው ድምፅ ለሁለት እኩል የተከፈለ ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ድምፅ አሸናፊ ይሆናል፣

ሸ) በዚህ ደንብ በተለየ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር የየትኛውም የፓርቲው መዋቅር ምልዐተ-ጉባኤ ተሟልቷል የሚባለው ከጠቅላለው የጉባኤው ወይም የስብሰባው 50%+1 እና ከዚያ በላይ ሲገኙ ነው፣

ቀ) በሁሉም ስብሰባዎች በተለይም አስቸኳይ ስብሰባዎች ሁሉም የሚመለከታቸው አባላት የመገኘት ግዴታ አለባቸው። ሆነ ብሎ ምልዐተ ጉባኤ እንዳይሟላ ማድረግ የተከለከለ ነው። ምልዐተ ጉባኤ እንዳይሟላ ያደረገ በዲስፕሊን ጥፋት ይጠየቃል።

በ) በየትኛውም ደረጃ በተወሰነ ውሳኔ ላይ ከተሰብሳቢ አባላት መካከል 1/3ኛ የሚሆኑት እንደገና እንዲታይ ጥያቄ ካቀረቡ ፤ጥያቄው ለውይይት ክፍት ሆኖ እንደገና ውሳኔ ይሰጥበታል።

ተ) በአንድ መድረክ ላይ በተወሰነ ውሳኔ ላይ አቤቱታ ቀርቦ ውሳኔው በድጋሚ በዚያው መድረክ ተቀባይነት ካገኘ በድጋሜ አቤቱታ አይቀርብም። በጉዳዩ ላይ አቤቱታ ማቅረብ የሚቻለው በተግባር እየፈፀሙ በሂደት በሚከፈት የጉባኤ (ኮንፈረንስ) አጋጣሚ ወይም የፅሁፍ ፊርማ በማሰባሰብ ብቻ ይሆናል።

ቸ) እንደገና ይታይልን የሚል ጥያቄ ሲቀርብ የወሰነው አካል በጉባኤ ላይ ከሆነ በቃል ወይም በፅሁፍ አቤቱታው ቀርቦ ጉዳዩ ከላይ በተቀመጠው መሰረት ይታያል። ወሳኙ አካል ጉባኤው/ስብሰባው ፈፅሞ ከተበተነ በኋላ ግን አቤቱታ ሊቀርብ የሚችለው በፅሑፍ ብቻ ይሆናል።

ኀ) አቤቱታ አቅራቢው አቤቱታውን በፅሁፍ አዘጋጅቶ ለሰብሳቢው ያቀርባል። ሰብሳቢው አቤቱታውን ወደሚመለከታቸው አባላት ሁሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ በማሰራጨት አቤቱታውን የሚደግፉ ሁሉ እንዲፈርሙ ያደርጋል። ከሚመለከታቸው አባላት ውስጥ 1/3ኛው ከፈረሙ ፤ጉዳዩ በሚቀጥለው መደበኛ ወይም አስቸካይ ስብሰባ ላይ እንዲታይ ይደረጋል።

ነ) ሁሉም የፓርቲው አሰራሮች በግልፀኝነትና ዴሞክራሲያዊነትን ላይ የተመሰረቱ ይሆናሉ።

ኘ) የፓርቲው ከፍተኛ የአመራር አካላት የሚወሰኑና በሀገሪቱና በህዝቦቿ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ የሚያሳርፉ አቋሞችና ውሳኔዎች ሁሉ ውሳኔውን ባስተላለፈው አካል በሚስጢር ተጠብቆ እንዲቆይ ካልተወሰነ በስተቀር ከአስፈላጊው ማብራሪያ ጋር ለአባላትና እንደአስፈላጊነቱ ለሕዝብ ይገለፃሉ።

አ) በፓርቲው ጉባኤዎች፤ኮንፈረንሶችና ስብሰባዎች የሚተላለፉ ውሳኔዎች እና አቅጣጫዎች በቃለ ጉባኤ ተይዘው ፣ፀድቀው ይቀመጣሉ።

ከ) በልዩ ሁኔታ በምስጢርነት ተጠብቀው ሊቆዩ የሚችሉ የፓርቲ ጉዳዮች የሚለዩበት አሰራር ይዘረጋል።

ኸ) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ አመራር አካላት ለወሰኗቸው ውሳኔዎች በተናጠልና በጋራ በሙሉ ኃላፊነት ይወስዳሉ። በተጨማሪም ኃላፊነትን ያለመወጣት ወይም ከተሰጠ ኃላፊነት ውጪ መሰማራት ተጠያቂነትን ያስከትላል።

ወ) ተጠያቂነትም እንደሁኔታው በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ወይም በሀገሪቱ ሕጎች መሰረት ፖለቲካዊ ፤አስተዳደራዊ ወይም ሕጋዊ እርምጃዎችን ያስወስዳል።

ዐ) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲው አካላት የስራ እንቅስቃሴያችውን የሚያሳይ ዝርዝር እቅድና ሪፖርት በወቅቱ የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፤የበላይ አካላትም ወቅታዊ ግብረ መልስ መስጠት አለባቸው።

ዘ) አባላትና አደረጃጀቶች የስራ አፈፃፀም ውጤታማነታቸውን የሚመዘኑባቸውና እርስ በርስ የሚማማሩባቸው መደበኛ የውይይት ጊዜያት ይኖራቸዋል።

ዠ) ፓርቲው አባላቱን አመራሩንና መዋቅሩ ላሳዩት የላቀ አፈፃፀም ዕውቅናና ሽልማት የሚሰጥበት የአሰራር ስርዓት ይከተላል።

የ) ፓርቲው በሁሉም ደረጃዎች የወጣቶችና የሴቶች አደረጃጀቶችን የማሳተፍና የማብቃት አቅጣጫና አሰራርን ይከተላል።

ደ) ፓርቲው ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የሚኖረው ግንኙነቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ ላሉት በማዕከላዊነት የሚወሰን ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ከዚያ በታች ባሉት የፓርቲው አደረጃጀት ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል።

ጀ) ልዩ ድጋፍ የሚሹና አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የፓርቲው አባላትና አደረጃጀቶች በየደረጃው ተገቢውን ውክልና እንዲያገኙና የአዎንታዊ እርምጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል። ዝርዝር መመሪያ በማዕከላዊ ኮሚቴ የሚወጣ ይሆናል።

ገ) የፓርቲው ዓላማዎች፣ ፕሮግራምና ዕቅድ ተግባራዊ የሚሆኑት በፓርቲው ዋና ፅ/ቤት፣ በክልል፣ በከተማ አስተዳደርና በየደረጃው ባሉ የፓርቲ ፅ/ቤቶች የፓርቲ አደረጃጀቶች እና በውጪ ሀገር በሚኖሩ የፓርቲው መዋቅሮች አማካኝነት ይሆናል።

ጠ) በፓርቲው አባላትና እጩ አባላት በሚፈፀሙ ጥፋቶች ላይ የሚወሰደው የዲስፕሊን እርምጃ የፓርቲውን ስነ-ምግባር ለማዳበር፣ ስህተቶችንና ጉድለቶችን ለማረምና የፓርቲውን ጥራትና ጥንካሬ ለመጠበቅ የሚያገለግል ሊሆን ይገባል።

## አንቀፅ ስምንት - የፓርቲው ምርጫ መርህና የአሰራር ስርዓት

1. የፓርቲው የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት፣ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት፣ የፕሬዝዳንት፣ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ የምክትል ፕሬዝዳንቶች እና የኢንስፔክሽንና ስነ-ምግባር ኮሚሽን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ፀሐፊ አመራር ምርጫ ግልፅ፣ ነፃና ፍትሃዊ በሆነ ሁኔታ በሚስጢር በሚሰጥ ድምፅ የሚመረጡ ይሆናል፣
2. በፓርቲው ውስጥ በሃላፊነት ቦታዎች የሚደረጉ ምርጫዎች የፆታ ተዋፅኦን የጠበቁ መሆን ይኖርባቸዋል፤
3. ማንኛውም የፓርቲ አባል በዚህ ደንብ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ (8)(ሰ) በወጣው የፓርቲ የምርጫ የአሰራር ስርዓት መሰረት በአገሪቱ በሚካሄዱ የጠቅላላ፣ የአካባቢ፣ የማሟያና የድጋሚ ምርጫዎች ፓርቲውን ወክሎ የመወዳደር መብት አለው።

# ምዕራፍ ሁለት

## II. አባልነት

### አንቀፅ ዘጠኝ - የፓርቲው አባል ስለመሆን

1) ከዚህ በታች የተመለከቱትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የፓርቲው አባል መሆን ይችላል
   ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ተቀብሎ በፅናት ተግባራዊ ለማድረግ ፍቃደኛ የሆነ፣
   ለ) መልካም ስነ-ምግባር ያለውና በህብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነት ያለው፣
   ሐ) በህብረ-ብሔራዊነት እና በሀገራዊ አንድነት ላይ ፅኑ አቋም ያለውና ዋልታ-ረገጥ አመለካከትና ተግባሮችን በፅናት የሚታገል፣
   መ) ዜጎችንና ሕዝቦችን በእኩልነት የሚያገለግል፣ የሕዝብ ጥቅምን የሚያስቀድም፣ ከሙስናና ብልሹ አሰራሮች ራሱን ያራቀና ሌሎችንም የሚታገል፣
   ሠ) የፓርቲውን ዕሴቶችና ዓላማዎችን ተቀብሎ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ቁርጠኛ የሆነ፣
   ረ) ወርሃዊ የአባልነት ክፍያ ለመክፈል ፍቃደኛ የሆነ፣
   ሰ) እድሜ 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ፣
   ሸ) የሌላ ፖለቲካ ፓርቲ አባል ያልሆነ፣
   ቀ) የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን መብቱ በሕግ ያልተገደበ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተገፈፈ፣
   በ) በዚህ ደንብ በተወሰነው መሰረት የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ የፓርቲው አባል መሆን ይችላል።
2) የአባልነት የዕድሜ ጣሪያን እና የክብር አባልነትን የተመለከተ ዝርዝር አፈፃፀም መመሪያ በማዕከላዊ ኮሚቴው ይወጣል።

### አንቀፅ አስር - ለአባልነት የሚቀርብ ጥያቄ

1) አንድ የፓርቲው አባል ለመሆን የወሰነ ዜጋ በአካባቢው ለሚገኘው የፓርቲው ፅሕፈት ቤት ማመልከት ይኖርበታል።

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በየደረጃው የሚገኝ የፓርቲው መዋቅርና አባል ለፓርቲው ፕሮግራምና መተደደሪያ ደንብ ታማኝና ለተግባራዊነቱም ይታገላል ብሎ ያመነበትን ግለሰብ ለፓርቲው አባልነት ሊመለምለው ይችላል።

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሰረት መስፈርቱን አሟልቶ የተመለመለ ግለሰብ ለስድስት ወራት በሙከራ አባልነት ይቆያል።

4) የፓርቲው ሕዋስ የአንድ እጩ አባል አፈፃፀም አይቶ ሙሉ አባል የማድረግ ወይም ተጨማሪ ከሶስት ወራት ላልበለጠ ጊዜ የእጩነት ቆይታ እንዲራዘም ለመሰረታዊ ድርጅት የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል። በመሰረታዊ ድርጅቱ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ዕጩ አባል አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ለሚገኘው አደረጃጀት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

5) የእጩ አባልነት ቆይታ ከአንድ ጊዜ በላይ አይራዘምም፤ ከክትትል ሂደትም ይሰረዛል።

6) እጩ አባሉ በሙከራ ጊዜ ቆይታው ፓርቲው የሚሰጠውን ተልዕኮ ይፈፅማል።

7) የአባላት ምልመላ፣ ግንባታ፣ ምደባ፣ ምዝናና ስንብት ዝርዝር መመሪያ በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ይወጣል።

## አንቀፅ አስራ አንድ - የአባል መብት

1) ማንኛውም የፓርቲ ሙሉ አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል

ሀ) በፓርቲው አካላት ምርጫዎች የመምረጥና የመመረጥ፣

ለ) በፓርቲው ጉባኤዎች የመሳተፍ፣ በውይይት የመካፈልና በድምፅ በሚወሰኑ ጉዳዮች ላይ ድምፅ የመስጠት፣ በማንኛውም ጉዳይ ላይ በሕጋዊ መድረኮች ሐሳቡን በፅሑፍም ሆነ በቃል የማቅረብ፣

ሐ) በማንኛውንም የፓርቲ አካል ወይም አባላት ላይ በተቻለ መጠን በመረጃ የተደገፈ ገንቢ ሂስ የማቅረብ፣

መ) በየትኛውም የፓርቲ ውሳኔ ቅር ከተሰኘ ቅሬታውን በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በየደረጃው ለሚመለከተው አካል የማቅረብ፣

ሠ) ስለራሱ፣ ስለአካል፣ ስለፓርቲው ማወቅ የሚገባውን ነገር እስከ ፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ የመጠየቅና መልስ የማግኘት፣

ረ) የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ ፕሮግራም፣ አቋሞችና ውሳኔዎች ለሌሎች የማሳወቅ፤ የማስተዋወቅ፤ የማስረፅና በተጨባጭ እንዲተገበር የማድረግ እና፤

ሰ) በየትኛውም ጊዜ በፅሁፍ አመልክቶ እና በእጆቹ የሚገኙ የፓርቲው ንብረቶችን ኃላፊነት በተሞላበት አግባብ አስረክቦ መልቀቅ ይችላል።

2) ማንኛውም እጩ አባል በየደረጃው ለፓርቲው አካላት የመምረጥና የመመረጥ እንዲሁም ድምፅ የመስጠት መብት የለውም፣ የሌሎች የአባልነት መብቶች ግን ተጠቃሚ ነው፤ የግዴታዎችም ተገዥ ይሆናል።

## አንቀፅ አስራ ሁለት - የአባልነት ግዴታ

ማንኛውም የፓርቲ አባል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1) በማንኛውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ በፓርቲ ሕግ መሰረት የፀደቁትን የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና ዕቅዶችን የማወቅ፣ የመቀበል፣ የማክበር፣ የመገዛት እና ለተግባራዊነታቸው በግንባር ቀደምትነት የመታገል፣
2) በሚገኝበት የስራ መስክ እና ኃላፊነት ደረጃ የፓርቲውን አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ፣ የፓርቲውን የፖለቲካ ዕሳቤዎች ለመጠበቅ ሙሉ ተሳትፎ የማድረግ፣
3) የፓርቲውን መርሆዎች፣ እሴቶችና የአባላትን የስነ-ምግባር ሕጎችን የማክበር እና የፓርቲውን የህዝብና የሀገርን ደህንነትና ሉዓላዊነት የመጠበቅ፣
4) የሀገሪቱን ሕጎች እና ልዩ ልዩ መንግስታዊ ውሳኔዎችን ማክበር
5) የፓርቲውን አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ የሚጎዱ ማናቸውንም ዝንባሌዎችና ድርጊቶችን የማጋለጥና የመታገል፣
6) በፓርቲው ውስጥ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች የተያዙ ተናጠል አቋሞችን የፓርቲው በማስመሰል በማናቸውም መልኩ በሚዲያ ከማሰራጨት የመቆጠብ፣
7) በአባላት መካከል የሚኖረውን መልካም ግንኙነት ከሚያጎድፍ ድርጊቶች የመታቀብ፣
8) በዚህ ደንብ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 8/ተ/ እንደተገለፀው ማዕከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው የአባልነት መዋጮ ዓይነትና አከፋፈል መመሪያ መሰረት የአባልነት መዋጮ የመክፍል፣
9) የፓርቲውን ንብረት በአግባቡ የመጠበቅ፣
10) ከሙስና የፀዳ፣ መስናንና አድሎአዊ አሰራርን የመታገልና የማጋለጥ ግዴታ እና

11) ከአንድ አካባቢ ወይም የስራ ቦታ ወደ ሌላ አካባቢ ወይም የስራ ቦታ በቋሚነት ለቅቆ ሲሄድ የለቀቀበትን እና የደረሰበትን የፓርቲ መዋቅር ማሳወቅ፣ የፓርቲውን ንብረት እና ሰነዶችን ለለቀቀበት አካባቢ የፓርቲ መዋቅር ማስረከብ አለበት።

## አንቀፅ አስራ ሶስት - በአባላት ላይ በዲስፒሊን ጉድለት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

1) ማንኛውም አባል በሚከተሉት ሁኔታዎች ከቃል ማስጠንቀቂያ ጀምሮ ከአባልነት እስከ ማሰናበት የሚያደርስ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡

ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ያላከበረ ወይም ሌሎች ጥፋቶችን የፈፀመ አባል ወይም እጩ አባል ጉዳዩ በዝርዝር ታይቶ እንደ ጥፋቱ ክብደት የዲስፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል።

ለ) ማንኛውም አባል የፓርቲውን የአባልነት መዋጮ በተከታታይ ለ6 ወራት አሳማኝ ባልሆነ ምክንያት ካልከፈለ እና ውዝፍ መዋጮውን ለመክፈል ፍቃደኛ ካልሆነ ከአባልነቱ በራሱ ፈቃድ እንደለቀቀ ይቆጠራል።

ሐ) ማንኛውም አባል በትክክለኛ መረጃ ላይ ሳይመሰረት አባላትን ከመለመለ ወይም ከአባልነት ካገለለ፣ አባላትን ከወነጀለ በዲስፕሊን ጥፋት ይጠየቃል።

መ) ማንኛውም አመራር ወይም አባል የሐሰት ሪፖርት መስጠትም ሆነ መጠቀም ክልክል ነው።

ሠ) በፓርቲው ውስጥ አንጃነት እና ቡድንተኝነት መፍጠር ወይም ማስፋፋት ክልክል ነው።

ረ) ማንኛውም አባል የሌላ ፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆኑ ከተደረሰበት ከፓርቲ አባልነቱ ይሰረዛል።

ሰ) የፓርቲው አባላትና እጩ አባላት የሚፈፅሟቸው ጥፋቶች ክብደት እየታየ የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

- **ለሙሉ አባል**

  ሀ/ ተግሳፅ፣

  ለ/ የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት፣

  ሐ/ የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣

  መ/ ከኃላፊነት ማገድ፣

  ሠ/ ከኃላፊነት ማነሳት፣

ረ/ ከአባልነት ማገድ፣

ሰ/ ከአባልነት መሰረዝ፣

- **ለእጩ አባል**

ሀ/ የእጩ አባልነት ለአንድ የሙከራ ጊዜ ማራዘም፣

ለ/ ከእጩ አባልነት መሰረዝ፣

ሸ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እርምጃ የተወሰደበት አባል ወይም እጩ አባል አቤቱታውን በየደረጃው ላለው የፓርቲ መዋቅር አቅርቦ በውሳኔው ካልረካ በየደረጃው ላለው የፓርቲ የኢንስፔክሽንና ስነ-ምግባር ኮሚሽን ሊያቀርብ ይችላል፤

- **የአባላት የዲስፒሊን ጉደለት እርምጃ አወሳሰድ ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይፈፀማል፡፡**

# ምዕራፍ ሶስት

## III. የፓርቲው አወቃቀርና አደረጃጀት

### አንቀፅ አስራ አራት - የፓርቲ አወቃቀርና የአመራር አካላት

1) የፓርቲው ድርጅታዊ አወቃቀር የአገሪቱን ህገ-መንግስታዊ ፌዴራላዊ አወቃቀር የተከተለ ነው። በዚሁ መሰረት የፓርቲው ድርጅታዊ አወቃቀር የሚከተሉት ናቸው።

   ሀ) ፌዴራል፣

   ለ) ክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ

   ሐ) ዞን/ከተማ/ክፍለ ከተማ/ልዩ ወረዳ/ቀበሌ፣

   መ) ወረዳ//ከተማ/ክፍለ ከተማ፣

   ሰ) ቀበሌ ናቸው።

2) ፓርቲው የሚከተሉት ተቋማዊ መዋቅሮች ይኖሩታል።

   ሀ) ጉባዔ፣

   ለ) ማዕከላዊ ኮሚቴ፣

   ሐ) ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣

መ) ፕሬዝዳንት፣

ሰ) ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንቶች፣

ረ) የኢንስፔክሽና የስነ-ምግባር ኮሚሽን፣

ሰ) የፓርቲው ዋና ፅህፈት ቤት

ሸ) የፓርቲው የክልል ፓርቲ ፅህፈት ቤቶች፣

ቀ) የብልፅግና የሴቶች ሊግ

በ) የብልፅግና የወጣቶች ሊግ

ተ) የፓርቲው የአካባቢ አካላት

3) የፓርቲው መሰረታዊ ድርጅትና ሕዋሳት አባላት በሚገኙበት ቦታዎች ይቋቋማሉ።

## አንቀፅ አስራ አምስት - የፓርቲው ጉባዔ፣ የክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ፣ የዞን፣ የከተማ፣ የወረዳና የቀበሌ የኮንፈረንሶች አወቃቀር

1) የፓርቲው ጉባዔ በፌዴራል ደረጃ ይቋቋማል፣
2) በክልል ደረጃ ክልላዊ ኮንፈረንስ የሚኖር ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በየደረጃው ከዞን እስከ ቀበሌ ኮንፈረንሶች ሊዋቀር ይችላል።
3) የኮንፈረንስ ውክልና በዋናነት የአባላትን ብዛት መሰረት ያደረገ ሆኖ አነስተኛ የህዝብ ብዛት ቁጥር ያላቸውን የብሔር ብሔረሰብና ህዝቦች አባላት ውክልና ባረጋገጠ መልኩ ይዋቀራል።
4) በመደበኛ ጉባዔና በእያንዳንዱ ኮንፈረንስ ወቅት የሚመረጡ ጉባዔተኞች እና የኮንፈረንስ ተሳታፊዎች ብቃት ያላቸው አዳዲስ አባላት ያካተተ ይሆናል።

## አንቀፅ አስራ ስድስት - የፓርቲው ጉባዔ

1) የፓርቲው ጉባዔ የፓርቲው ከፍተኛ የአመራር አካል ነው።
2) የፓርቲው ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ በሁለት ዓመት ተኩል አንድ ጊዜ ይካሄዳል፣ የጉባኤው የመካሄጃ ጊዜ ከሶስት ዓመት መብለጥ የለበትም።
3) ፕሬዝዳንቱ የጉባኤው ሰብሳቢነት፣ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ደግሞ ምክትል ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላሉ።
4) የጉባኤው ተሳታፊዎች ቁጥር ከ500 በላይ ሆኖ፤ ስብጥሩ ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ልዩ ድጋፍ የሚሹና አነስተኛ የህዝብ ቁጥር ያላቸውን

የህብረተሰብ ክፍሎች ውክልና እንዲያገኙና የአዎንታዊ እርምጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚያስችል መልኩ ይፈፀማል።

5) የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ቢያንስ $^{1}/_{3}$ በድምፅ ብልጫ ሲወስን በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።
6) የፓርቲው ኢንስፔክሽንና ስነምግባር ኮሚሽን የቋሚ ጉባኤ አባላት $^{1}/_{3}$ የድጋፍ ድምፅ ካገኘ አስቸኳይ ሰብሰባ እንዲጠራ ሊያደረግ ይችላል።
7) የፓርቲው ጉባኤ አስቸኳይ ስብሰባ ሲጠራ ቀድሞ በተካሄደው መደበኛ ጉባኤ የተካፈሉት ጉባኤተኞች በቀጥታ ይሳተፋሉ።
8) ለመደበኛ የፓርቲው ጉባኤ ከአባላቱ መካካል ቢያንስ $^{2/}_{3}$ በስብሰባው ላይ ሲገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል።
9) የአስቸካይ ጉባኤ ስብሰባ ምልዐተ ጉባኤ 50%+1 ነው።
10) የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ እና ማዕከላዊ የኢንስፔክሽና ስነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት በቀጥታ በጉባኤው ስብሰባ ይሳተፋሉ።
11) የፓርቲው ጉባዔ አባላት ውክልናና ተሳትፎ የህዝብና የአባላትን ቁጥር መሰረት ያደረገ ሆኖ ዝርዝሩ ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል።
12) ለመደበኛ ጉባኤ እና አስቸኳይ ጉባኤ የጉባኤዎቹ ጊዜ፣ ቦታና አጀንዳዎችን አስቀድሞ በፓርቲው ዋና ፅሕፈት ቤት በኩል መገለፅ አለበት።

## አንቀፅ አስራ ሰባት - የፓርቲው ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት፣

1) የፓርቲው ጉባኤ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤-
   ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣ እንደአስፈላጊነቱ ይቀይራል።
   ለ) ፓርቲው የሚመራባቸውን አጠቃላይ አቅጣጫዎችና ውሳኔዎች ያስቀምጣል፣
   ሐ) የኢንስፔክሽንና ስነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት ቁጥር ይወስናል፣
   መ) የማእከላዊ ኮሚቴ፣ የኢንስፔክሽንና ስነ-ምግባር ኮሚሽንና እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች አካላት የሚቀርቡለትን ሪፖርቶችን ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ያፀድቃል።
   ሰ) ፓርቲው ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር የሚያደርገውን የውህደት ወይም የቅንጅት ወይም ግንባር የመፍጠር የውሳኔ ሀሳብ ያፀድቃል።

ረ) የማዕከላዊ ኮሚቴ እና የኢንስፔክሽንና ስነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት ዕገዳና ስንብት ላይ ውሳኔ ይሰጣል።

ሰ) የፓርቲውን ስምና ዓርማ ያፀድቃል፣ ያሻሽላል፣ ይለውጣል።

ሸ) ጉባኤው መደበኛ ስራውን ከመጀመሩ በፊት በዝግጅት ኮሚቴ የሚቀርብለትን የጉባኤ ዝግጅት ሪፖርትና የስብሰባውን የስነ-ስርዓት ደንብ መርምሮ ያፀድቃል።

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባኤው ከተግባርና ኃላፊነቱ በሙሉ ወይም በከፊል ለማዕከላዊ ኮሚቴ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## አንቀፅ አስራ ስምንት - የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ፣

1) የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ጉባኤው ሆኖ ከጉባኤ እስከ ጉባኤ ፓርቲውን የሚመራ ከፍተኛ አካል ነው።

2) ማዕከላዊ ኮሚቴው በቀጥታ በነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ከጉባኤው አባላት በሚስጢር ድምፅ አሰጣጥ በሚመረጡ አባላት የሚመሰረት ነው።

3) የማዕከላዊ ኮሚቴው አባላት ብዛትና ስብጥር በሕዝብ ብዛት እና በአባላት ቁጥር መሰረት ሆኖ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ በማዕከላዊ ኮሚቴ ይወጣል።

4) ማእከላዊ ኮሚቴው በየስድስት ወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ካመነበት ወይም ከማዕከላዊ ኮሚቴው አባላት መካከል $^{1}/_{3}$ ያህሉ ሲጠይቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

5) የማዕከላዊ ኮሚቴ ምልዐተ ጉባኤ ከአባላቱ ከ50%+1 የተገኙበት ይሆናል።

6) በማዕከላዊ ኮሚቴ የተላለፈ ማንኛውም ውሳኔ ከፓርቲው ኢንስፔክሽን እና ስነ-ምግባር ኮሚሽን ውጪ በሁሉም የፓርቲው መዋቅሮችና አካላት ተፈፃሚ ይሆናል።

7) ማዕከላዊ ኮሚቴ በፓርቲው ፕሬዝዳንት እና በተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንቱ በጋራ ይመራል።

8) ማዕከላዊ ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ፣ የጉባኤው ውሳኔዎች ስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።

ለ) በፓርቲው ጉባኤ በሚቀመጠው አቅጣጫና ውሳኔዎች መሰረት ፓርቲውን በበላይነት ይመራል፣ የፓርቲውን አጠቃላይ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣

አቅጣጫዎችና እቅዶችን እንዲሁም የማስፈፀሚያ መመሪያዎችን ያመነጫል፣ አፈፃፀማቸውን በየጊዜው ይገመግማል።

ሐ) የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴን ሪፖርት ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ውሳኔ በሚሹ ነጥቦች ላይ ይወስናል።

መ) በፓርቲው ፕሬዝዳንት የተፈፀመን የስምምነት የውሳኔ ሐሳብ ያፀድቃል፤

ሠ) የፓርቲውን የምርጫ የአሰራር ስርዓት መመሪያ ያወጣል።

ረ) የምርጫ ስትራቴጅ ያፀድቃል፤ ለምርጫ የሚደረገውን ሂደት የሚመራ የምርጫ ኮሚቴ ያቋቁማል።

ሰ) አስፈላጊ የሆኑ የፓርቲ መዋቅሮችን ይዘረጋል።

ሸ) የማዕከላዊ ኮሚቴ እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን ቁጥርና ስብጥር ይወስናል።

ቀ) ከአባላቱ መካከል የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት፣ የፓርቲውን ፕሬዝዳንት፣ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንቶች ይመርጣል።

በ) የማእከላዊ ኮሚቴውን ዓመታዊ የስራ እቅድና የፓርቲውን በጀት ያፀድቃል።

ተ) የፓርቲ አባላት የመዋጮ ዓይነት፣ መጠንና አከፋፈል በተመለከተ መመሪያ ያወጣል።

ቸ) በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ትርጓሜ ላይ ለሚነሱ ክርክሮች ውሳኔ ይሰጣል።

ነ) የፓርቲውን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራትን ሁሉ ያከናውናል።

ኘ) ለፓርቲው ፕሮግራምና ደንብ ተገዢ ያልሆኑና የአመራር ብቃት የጎደላቸውን የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላትን $^{2}/_{3}$ ድምፅ ያግዳል።

አ) ደንቡን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ዝርዝር መመሪያዎችን ያፀድቃል፤

9) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /8/ /ሀ-ከ/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማዕከላዊ ኮሚቴው ከተግባርና ኃላፊነት በከፊል ለፓርቲው ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## አንቀፅ አስራ ዘጠኝ - የፓርቲው ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፤-

1) የፓርቲው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለማእከላዊ ኮሚቴ ሆኖ ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት መካከል በምስጢር ድምፅ ይመረጣል።

2) የስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ በፓርቲው ፕሬዝዳንት ይመራል።

3) የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባውን በሶስት ወር አንድ ጊዜ ያደርጋል።

4) የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አስቸኳይ ስብሰባ በፕሬዝዳንቱ ወይም ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት $^{1}/_{3}$ ያህሉ ከጠየቁ ከዚህ ባነሰ ጊዜ ሊጠራ ይችላል።

5) የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ምልዐተ ጉባኤ ከአባላቱ ከ50%+1 የተገኙበት ይሆናል።

6) የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

   ሀ. በጉባኤውና በማዕከላዊ ኮሚቴ የሚወጡ እቅዶች፣ አቅጣጫዎች፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች መከበራቸውንና በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ አመራር ይሰጣል፤

   ለ. የጉባኤውንና የማዕከላዊ ኮሚቴውን አቅጣጫዎችና ውሳኔዎች መሰረት በማድረግ የህብረተሰቡ ኑሮ እንዲሻሻልና አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመፍጠር እንዲቻል አስፈላጊውን ስልት ይቀይሳል፤ መመሪያ ይሰጣል፤ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፤

   ሐ. ህብረ-ብሔራዊ አንድነታችንን የሚያጠናክርና የፌዴራል ስርዓቱን የሚያጎለብት የፖሊሲ ሐሳቦችን ያመነጫል፤ መተግበራቸውን ይከታተላል።

   መ. የጉባኤውንና የማዕከላዊ ኮሚቴ ውሳኔዎች ህገ-ደንቡን መሰረት በማድረግ የፓርቲውን የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲ የበለጠ ለማዳበር የሚያስችሉ መመሪያዎችን ከኢንስፔክሽን እና ስነ-ምግባር ኮሚሽን ጋር በመመካከር ያወጣል፤ ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል።

   ሠ. ለማዕከላዊ ኮሚቴው የስራ ዕቅድና ሪፖርት ያቀርባል።

   ረ. በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ አመራር የስራ እንቅስቃሴ ይመራል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል።

   ሰ. ለፓርቲው ፅ/ቤት የዕለት ተዕለት የስራ መመሪያ ይሰጣል።

   ሸ. በፓርቲው የአመራር መዋቅር የአመራር ምደባ ያካሂዳል፤ የአፈፃፀም መመሪያ በማውጣት ይፈፅማል።

   ቀ. የፓርቲ ጉባኤ አዘጋጅ ኮሚቴ ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና ከኢንስፔክሽንና ስነ-ምግባር ኮሚሽን በተውጣጡ አባላት ያዋቅራል፡፡

   በ. የማዕከላዊ ኮሚቴ አጀንዳ ያዘጋጃል።

ተ. የፓርቲው ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎችና ውሳኔዎች ለፓርቲው አባላት እና ለመላው ሕዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ስልት ይቀይሳል ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል።

7) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /6/ ከሀ-በ/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ከተግባርና ኃላፊነቱ በከፊል ለፓርቲው ፕሬዝዳንት ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## አንቀፅ ሃያ - የፓርቲው ፕሬዝዳንት

1) የፓርቲው ፕሬዝዳንት ተጠሪነቱ ለማዕከላዊ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

   ሀ) የማእከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሰባዎችን በሰብሳቢነት ይመራል፣

   ለ) የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስራዎችን ያስተባብራል ፣

   ሐ) የማዕከላዊ ኮሚቴና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎችን ያስፈፅማል፤

   መ) ፓርቲውን በመወከል ከተለያዩ አካላት ጋር የስራ ግንኙነት ያደርጋል፤ ስምምነቶችን ይፈርማል።

   ሰ) የስራ ሪፖርቱን ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ያቀርባል።

   ረ) ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባዎች አጀንዳ ያዘጋጃል፤

   ሰ) በማዕከላዊ ኮሚቴው እና በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## አንቀፅ ሃያ አንድ - የፓርቲው ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት

1) ፓርቲው አንድ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት እና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ተጨማሪ ምክትል ፕሬዝዳንቶች ይኖሩታል፤ የምክትል ፕሬዝዳንቶች ብዛት በማዕከላዊ ኮሚቴ የሚወሰን ይሆናል፤

2) ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ተጠሪነቱ ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፤

   ሀ/ ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ተክቶ ይሰራል።

   ለ/ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና በፕሬዝዳንቱ በሚሰጣቸው የስራ ስምሪት መሰረት ስራቸውን ያከናውናሉ፤

## አንቀፅ ሃያ ሁለት - የፓርቲው የኢንስፔክሽንና ስነ-ምግባር ኮሚሽን

1) የኢንስፔክሽንና ስነ-ምግባር ኮሚሽን ከፓርቲው ጉባኤ በሚመረጡ አባላት ይዋቀራል፤ የኮሚሽኑ አባላት ብዛት በጉባኤው የሚወሰን ሆኖ የህዝብ ብዛትና የአባላትን ቁጥር እንዲሁም አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎችን ውክልና እንዲያገኙና የአዎንታዊ እርምጃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሚያስችል አግባብ እንዲዋቀር ይደረጋል፤ ዝርዝሩ ማዕከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው በመመሪያ ይወሰናል፤
2) ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ጉባኤ ነው፣
3) የኮሚሽኑ አባላት ከስራቸው ጋር የሚያጋጭ የፓርቲ ምደባ አይሰጣቸውም፣
4) ኮሚሽኑ ቋሚ ፅሕፈት ቤት ተሿሚ አመራሮችና ተሿሚ ያልሆኑ ባለሙያዎች ይኖሩታል።
5) ኮሚሽኑ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲ አደረጃጀት ፅሕፈት ቤቶች ያደራጃል፣ የራሱን መዋቅር ይዘረጋል፤ አሰራራቸውም የሚከተለው ይሆናል፣
   ሀ) የክልልን እና የአካባቢ የኢንስፔክሽን እና ስነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት በየደረጃው በሚካሄዱ ኮንፈረንሶች ይመረጣሉ። ኮንፈረንስ እስከሚካሄድ ባለው ጊዜ የኮሚሽኑ አባላት መጓደል ሲያጋጥም ኮሚሽኑ ከየደረጃው ፓርቲ አመራር ኮሚቴ ጋር በመነጋገር ጊዜያዊ ምደባ ይሰጣል።
   ለ) የክልል እና የአካባቢ የኢንስፔክሽን እና ስነ-ምግባር ኮሚሽኖች አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ለሚገኘው የኮሚሽኑ መዋቅር ተጠሪ ይሆናሉ።
   ሐ) በፌደራልና በየደረጃው የሚኖሩ ክልላዊና አካባቢያዊ የኢንስፔክሽንና ስነ-ምግባር ኮሚሽን መዋቅሮች ባሉበት ደረጃ ካለ የፓርቲ አመራር ኮሚቴ ጋር በትብብር ይሰራሉ።
6) ኮሚሽኑ የሚከተሉት ተግባራት እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ) ኮሚሽኑ የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣
   ለ) የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራት እና የስነ-ምግባር ጤናማነት ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፤
   ሐ) የፓርቲው ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በአግባቡ መጠበቃቸውን ቁጥጥር ያደርጋል፤ የፓርቲው አባላት መዋጮ በወቅቱና በትክክል መሰብሰቡን ይቆጣጠራል፤

መ) የፓርቲው አባላትና አካላት መብቶች እና ጥቅሞች መከበራቸውን ይከታተላል፣

ሠ) ከአባላት የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ይቀበላል፤ ይመረምራል፤ የእርምት የውሳኔ ሐሳቡን ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና እንደአግባቡ በየደረጃው ላሉ የፓርቲ አመራር ኮሚቴዎች ያቀርባል፤

ረ) ዝርዝር የስነ-ምግባር፣ የኢንስፔክሽንና ቁጥጥር መመሪያ በማርቀቅ ለፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ አቅርቦ ያፀድቃል፣ ተፈፃሚነቱን ይከታተል፤

ሰ) የፓርቲ ስነ-ምግባርን ያሻሽላል፣ ሙስናን ለመዋጋት ጥረቶችን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፤

ሸ) በየደረጃው የስነ-ምግባር ጥሰቶችን ይመረምራል፣ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ቀ) ከፓርቲው የፖለቲካ አመራር ኮሚቴዎች በሚሰጥ ተልዕኮ መሰረት አስፈላጊ ሆነው የተገኙ የምርመራ፣ የክትትል እና የቁጥጥር ስራዎችን ይሰራል፤

በ) በፓርቲው አካላት መካከል ልዩነት ሲኖር ወይም ፓርቲውን የሚመለከቱና መጣራት የሚገባቸው ጉዳዮች ሲኖሩ እንዲሁም በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ወይም ስራ አስፈፃሚ በኩል ጥያቄ ሲቀርብለት እንደ አንድ ነፃ አጣሪ አካል ሆኖ ያገለግላል፤ የራሱን የውሳኔ ሀሳብ ያካተተ ሪፖርትም ለማዕከላዊ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

ተ) ኮሚሽኑ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንቡ የተሰጡትን ተግባራትና ሀላፊነቶች አስመልክቶ በየወቅቱ ኢንስፔክሽንና ልዩ ልዩ ጥናቶችን ያካሂዳል፡፡ የጥናቱን ግኝቶች ከውሳኔ ምክረ ሀሳብ ጋር ለሚመለከታቸው የፓርቲ አካላት ያቀርባል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፡፡

ቸ) ኮሚሽኑ ለስራረ የሚያስፈልገርረን አመታዊ በጀት ያፀድቃል፣ በኃላፊነት ያስተዳድራል፣ ይመራል፡፡

ኀ) ለፓርቲው ፕሮግራምና ህገ ደንብ ተገዢ ያልሆኑ የኮሚሽን አባላትን በ2/3ኛ ድምጽ ያግዳል፤

ነ) ስለስራው አፈፃፀም በፌደራል ደረጃ ለፓርቲው ጉባኤ፣ እንዲሁም እንደግባብነቱ በክልል እና አካባቢያዊ መዋቅሮች አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ላለው ኮሚሽን ሪፖርት ያቀርባሉ፣

ኘ) ይህን መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በማድረግ የኮሚሽኑን የውስጥ አሰራር መመሪያዎች ማውጣት ይችላል፤

አ) ይህን መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በማድረግ የኮሚሽኑን የውስጥ አሰራር መመሪያዎች ማውጣት ይችላል፣

7) የክልልና የአካባቢ የኢንስፔክሽን እና ስነ-ምግባር ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነቶች በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (6) ስር የተዘረዘሩት ይሆናሉ፣

8) ኮሚሽኑ በየሶስት ወሩ መደበኛ ስበሰባውን ያካሂዳል፤

9) ኮሚሽኑ የራሱን ዓመታዊ ዕቅዶች እያዘጋጀ ተግባራቱን ይመራል፤

10) በኮሚሽኑ የሚቀርበውን የእርምት ሃሳብ የስራ አስፈፃሚው ካልተቀበለው ለማዕከላዊ ኮሚቴው ይቀርባል፤ ማዕከላዊ ኮሚቴው በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ እስከ ጉባኤ ድረስ ተፈፃሚ ይሆናል፤

11) ኮሚሽኑ ከመካከሉ ሰብሳቢ፤ ምክትል ሰብሳቢና ፀሀፊውን መርጦ ለጉባኤው ያሳውቃል።

## አንቀፅ ሃያ ሶስት - የፓርቲው ዋና ፅ/ቤት

1) ፅሕፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ የፓርቲውን የፖለቲካ፣ የድርጅት፣ የህዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ይመራል፣ የጥናትና ምርምር ማዕከል ሆኖ ያገለግላል።

2) ፅሕፈት ቤቱ ኃላፊና ምክትል ኃላፊዎች ይኖሩታል፣

3) ፅሕፈት ቤቱ በየወቅቱ እቅድና ሪፖርት አዘጋጅቶ ለፕሬዝዳንቱ ያቀርባል፤

4) እጩ የክልል ፓርቲ ፅሕፈት ቤት ኃላፊዎችን፣ ከየክልሉ የፓርቲ አመራሮች ጋር በመሆን ከለየ በኋላ ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመመካከር ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለውሳኔ ያቀርባል፤

5) የዋናው ፅሕፈት ቤትንና የየደረጃውን የክልል ፓርቲ ፅሕፈት ቤቶችን ዝርዝር አሰራርን አስመልክቶ ለማዕከላዊ ኮሚቴ ረቂቅ መመሪያ ያቀርባል፤

6) ፅሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ/ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እቅዶችንና ሌሎች በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡ አቅጣጫዎችን መሰረት በማድረግ የፓርቲውን ስራዎች ያቅዳል፣ ያስፈፅማል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

ለ/ የፓርቲውን ገንዘብ፣ ንብረት እና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙ እና በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ የፓርቲውን የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየአመቱ በውጪ የሂሳብ ባለሞያ ወይም ኦዲተር እንዲመረመሩ እና እንዲረጋገጡ ያደርጋል።

ሐ/ የአባላት አደረጃጀት፣ የፖለቲካ ግንባታ፣ የህዝብና አለም አቀፍ ግንኙነት፣ የጥናትና ምርምርና ሌሎች ተግባሮችን ይፈፅማል።

መ/ በፕሬዝዳንቱ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ፓርቲውን ወክሎ ከሶስተኛ ወገኞች ጋር የስራ ግንኙነት ያደረጋል፡፤

ሰ/ ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመመካከር የፓርቲውን ልሳን ዋና አዘጋጅ እና የቦርድ አባላትን ይሰይማል፣

ረ/ የፀደቀውን የፓርቲ በጀት ያስተዳድራል፤

ሰ/ የፓርቲውን ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የስራ አፈፃፀም እና እቅዶችን በሚዲያና በህዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለህዝብ ያስተዋውቃል።

ሸ/ በፓርቲው ስም ውል ይዋዋላል፤ ይከሳል፤ ይከሰሳል።

ቀ/ በፓርቲው የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሰረት የፅሕፈት ቤቱን ሰራተኞች ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል።

በ/ የፓርቲ ጉባኤ ቦታ፣ ጊዜና አጀንዳ አዘጋጅቶ ሲወሰን ለሚመለከተው ፓርቲ አደረጃጀት ያሳውቃል።

ተ/ በፓርቲው አማካሪ ጉባኤ ስራዎችን ያስተባብራል።

ቸ/ በማዕከላዊ ኮሚቴ፣ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወይም በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል።

7) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /6/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ መመሪያ እንዲዘጋጅላቸው የተመለከቱና ሌሎች ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ዝርዝር መመሪያዎችን በፓርቲው አማካሪ ጉባኤ አማካኝነት በማስጠናት ለፕሬዝዳንቱ ያቀርባል።

8) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /6/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርቲ ዋና ፅሕፈት ቤቱ ከተግባርና ኃላፊነቱ ለክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ፓርቲ ፅሕፈት ቤቶች ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

# ምዕራፍ አራት

## IV. የፓርቲው የክልል አደረጃጀት

### አንቀፅ ሃያ አራት - የፓርቲ አደረጃጀትና አወቃቀር

1) ለፓርቲው ዋና ፅህፈት ቤት ተጠሪ የሆኑ፤ የክልል ፓርቲ ፅህፈት ቤቶች የክልል ስያሜ በመያዝ እንደሚከተለው ተቋቁመዋል።

   (ሀ) የብልፅግና ፓርቲ የኦሮሚያ ክልል ፅሕፈት ቤት

   (ለ) የብልፅግና ፓርቲ የአማራ ክልል ፅሕፈት ቤት

   (ሐ) የብልፅግና ፓርቲ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ፅሕፈት ቤት

   (መ) የብልፅግና ፓርቲ የሶማሌ ክልል ፅሕፈት ቤት

   (ሰ) የብልፅግና ፓርቲ የትግራይ ክልል ፅሕፈት ቤት

   (ረ) የብልፅግና ፓርቲ የአፋር ክልል ፅሕፈት ቤት

   (ሰ) የብልፅግና ፓርቲ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፅሕፈት ቤት

   (ሸ) የብልፅግና ፓርቲ የጋምቤላ ክልል ፅሕፈት ቤት

   (ቀ) የብልፅግና ፓርቲ የሐረሪ ክልል ፅሕፈት ቤት

   (በ) የብልፅግና ፓርቲ  የሲዳማ ክልል ፅሕፈት ቤት

   (ቸ) የብልፅግና ፓርቲ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ፅህፈት ቤት

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ለፓርቲው ዋና ፅህፈት ቤት ተጠሪ የሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬደዋ አስተዳደር ፓርቲ ፅህፈት ቤቶች ይቋቋማሉ፣ እንዲሁም በየደረጃው የክፍለ ከተማ እና የወረዳ/ቀበሌ አደረጃጀቶች ይኖራቸዋል።

3) ለክልል ፓርቲ ፅህፈት ቤት ተጠሪ የሆኑ የዞኖች፣ የወረዳዎች/ልዩ ወረዳዎች፣ የከተሞች ፅህፈት ቤቶች ይኖሩታል።

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እስከ (3) የተቋቋሙት ፅህፈት ቤቶች በየደረጃው የፓርቲ ኮንፈረንስ፣ አስተባባሪ ኮሚቴዎች፣ ፅህፈት ቤቶችና የኢንስፔክሽንና ስነ-ምግባር ኮሚቴ ይኖሯቸዋል፤

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተዘረዘሩት የክልል ፓርቲ ፅህፈት ቤቶች በተጨማሪ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 47 መሰረት በሚመሰረት ክልል ውስጥ ሁሉ ፓርቲው የክልል ፅህፈት ቤት ይኖረዋል።

6) በየደረጃው ያሉ የፓርቲው መዋቅሮች በክልሉ ያሉ የፓርቲውን አባላቶች በሙሉ የሚያሳትፉ እና የውህዳን ቡድኖችን ውክልና የሚያረጋግጡ ይሆናሉ።

## አንቀፅ ሃያ አምስት - የክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ፓርቲ ኮንፈረንስ የአሰራር ስርዓት፣

1) በየደረጃው የሚካሄደው የፓርቲው ኮንፈረንሶች የፓርቲ አባላት የፖለቲካ ግንባታ መድረክ ሆነው ያገለግላሉ፤

2) በየደረጃው ለሚካሄደው የፓርቲ ኮንፈረንሶች ውክልናና ስብጥር በአባላት ብዛት ይወሰናሉ፤

3) የፓርቲው ኮንፈረንሶች በየደረጃው በሚገኘው የፓርቲው አመራር ኮሚቴ ጠሪነት የሚሰበሰብ ሆኖ የክልል /አዲስ አበባና ድሬዳዋ/ በዓመት አንድ ጊዜ፤ የዞን፤ የወረዳ/ልዩ ወረዳና የከተማ ኮንፈረንሳቸውን በዓመት ሁለት ጊዜ፤ የቀበሌ በየሶስት ወሩ፣ መሰረታዊ ድርጅት ደግሞ በየወሩ ኮንፈረንሶች ይካሄዳሉ፣

4) የክልል የኢንስፔክሽን እና ስነ-ምግባር ኮሚሽን አጠቃላይ የስራ ሂደት እና ፖለቲካዊ ሁኔታ በክልል የፓርቲ ኮንፈረንሶች ላይ ይገመግማሉ፣

## አንቀፅ ሃያ ስድስት - የፓርቲ ኮንፈረንስ ተግባርና ኃላፊነት

1) በየደረጃው የፓርቲው ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣

2) የፓርቲው አቅጣጫዎች፣ ውሳኔዎችና ዕቅዶች በትክክል መተግበራቸውን ያረጋግጣል፣

3) የአባላቱን የፖለቲካ ብቃት እንዲዳብር ያደርጋል፣

4) በፓርቲው የጉባኤና የኮንፈረንስ ተሳትፎና ውክልና መመሪያ መሰረት ለፓርቲው ጉባኤ እና በየደረጃው ለሚካሄዱ ኮንፈረንሶች አባላትን ይወክላሉ፤

5) በየደረጃው ከፓርቲ አመራር ኮሚቴ እና ከኢንስፔክሽንና ስነ-ምግባር ኮሚቴ የሚቀርብለትን ዕቅድና የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ ያፀድቃል፤

6) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ኮንፈረንስ፣ የፓርቲው ጉባኤ፣ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ እና የፓርቲው ስራ አስፈፃሚ የሚያስቀምጡትን አጠቃላይ አቅጣጫ እና ውሳኔን ባከበረ መልኩ እና ሃገራዊ የሆኑት የፓርቲው አደረጃጀቶች በሚሰጡት የአመራር ማዕቀፍ ውስጥ ባሉበት የአስተዳደር ቀጠና ውስጥ የፓርቲው ትልቁ የፖለቲካ መድረክ ይሆናሉ።

## አንቀፅ ሃያ ሰባት - የፓርቲ ክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ /አካባቢ አመራር ኮሚቴ

1) የክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ፓርቲ አመራር ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፓርቲው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል፣
2) የዞን፤ የከተማ፣ የክፍለ ከተማ፣ ልዩ ወረዳ፣ ወረዳ/ከተማና ቀበሌ ፓርቲ ኮሚቴ አንድ ደረጃ ከፍ ብለው ለሚገኙት የፓርቲ አመራር ኮሚቴዎች ተጠሪ ይሆናሉ፤
3) የክልል፣ አዲስ አበባና ድሬዳዋ የፓርቲ አመራር ኮሚቴ በየወሩ አንድ ጊዜ፣ የዞን፣ የወረዳ/ልዩ ወረዳ፣ ከተማና ቀበሌ በወር ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋሉ፤
4) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲው አመራር ኮሚቴዎች የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል።
   ሀ/ በቀጠናቸው የፓርቲ የፖለቲካና የድርጅት ስራዎች በበላይነት ያስተባብራል፤
   ለ/ ከፓርቲው የበላይ አካላት የሚተላለፉ ውሳኔዎችንና መመሪያዎችን በተግባር ያውላሉ፣ ለስራው ዝርዝር የአፈፃፀም ፕሮግራም አውጥተው በስራ ላይ ያውላሉ፤
   ሐ/ ስለ ስራው ክንውን ቀጥሎ ላለው የፓርቲ አመራር ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባሉ፤
   መ/ በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ኮንፈረንሶች የሚያስቀምጡት አቅጣጫ፣ የፓርቲው ጉባኤ፣ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ እና የፓርቲው ስራ አስፈፃሚ የሚሰጡትን አመራር እና ውሳኔን ባከበረ መልኩ ተግባራዊ መሆናቸው ይከታተላል።
   ሠ) በሃገር አቀፍ ደረጃ ባሉ የፓርቲው መዋቅሮች የሚሰጡት አመራር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ክልላዊ እና አካባቢያዊ በሆኑ ጉዳዮች የፖሊሲ ሃሳብ ያመነጫል።
5) የክልልና አካባቢያዊ ፓርቲ አመራር ኮሚቴ አባላት ቁጥር ስብጥርና ምደባ ማዕከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል።

## አንቀፅ ሃያ ስምንት - የፓርቲ ፅህፈት ቤቶች

1) የፓርቲው ፅሕፈት ቤቶቹ በየደረጃው የፓርቲው የፖለቲካ፣ የድርጅትና የህዝብ ግንኙነት ማዕከል ሆነው ያገለግላሉ።
2) የፅህፈት ቤቶቹ ተጠሪነት አንድ ደረጃ ከፍ ብለው ለሚገኙ የፓርቲ ፅሕፈት ቤቶች ይሆናል።
3) ፅሕፈት ቤቶቹ በስራ አስፈፃሚ ወይም በየደረጃው ባሉት የፓርቲ አመራር ኮሚቴዎች የሚሰየሙ ኃላፊና ምክትል ኃላፊዎች ሊኖራቸው ይችላል፤
4) የፓርቲው ፅሕፈት ቤቶች የሚከተሉትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡-
   ሀ/ የክልሉን /አዲስ አበባና ድሬዳዋ/ የፓርቲ የፖለቲካና የድርጅት ስራዎች ያቅዳሉ፣ ያስፈፅማሉ፣ አፈፃፀሙን ይከታተላሉ፤
   ለ/ የፓርቲውን ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራሉ፣ በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፤
   ሐ/ የአባላት አደረጃጀት፣ የፖለቲካ ግንባታ፣ የሕዝብና አለም አቀፍ ግንኙነትና ሌሎች ተግባሮችን ይፈፅማሉ፤
   መ/ በፓርቲው ዋና ፅሕፈት ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ፓርቲውን ወክለው በየደረጃው ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋሉ፤
   ሰ/ በፓርቲው ዋና ፅሕፈት ቤት በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የፓርቲውን ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የስራ አፈፃፀም እና ዕቅዶችን በሚዲያና በሕዝብ ግንኙነት መሳሪያዎች ለሕዝብ ያስተዋውቃሉ፤
   ረ/ በፓርቲው የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሰረት የፅሕፈት ቤቱን ሰራተኞች ይቀጥራሉ፤ ያስተዳድራሉ፤ ያሰናብታሉ፤
   ሰ/ በየደረጃው ባሉት የፓርቲ አደረጃጀቶች የሚሰጡ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናሉ፤
   ሸ/ ፅሕፈት ቤቶቹ በየወቅቱ ዕቅድና ሪፖርት አዘጋጅተው በየደረጃው ላሉት የፓርቲ ፅሕፈት ቤቶች ሪፖርት ያቀርባሉ፤

## አንቀፅ ሃያ ዘጠኝ - የብልፅግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ

1) የብልፅግና የሴቶች ሊግ ዋነኛ ተልዕኮ በፓርቲው ውስጥም ሆነ ውጭ የሴቶች መብቶችና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ እና የኢትዮጵያና የህዝቦቿን

ሁለንተናዊ ብልፅግና ለማረጋገጥ ሴቶች የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲወጡ ለማስቻል የመሪነት ሚና መጫወት ነው።

2) የሴቶችን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ታሳትፎና ተጠቃሚነት ለማጎልበት የሴቶች የመታገያ መድረክና ድምፅ ሆኖ ያገለግላል።
3) የብልፅግና ፓርቲ አባል የሆኑ ሴቶች የብልፅግና ፓርቲ የሴቶች ሊግ አባል መሆን ይችላሉ፣
4) የብልፅግና የሴቶች ሊግ ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና የአሰራር መመሪያዎች በማይቃረን ሁኔታ የራሱ መተዳደሪያ ደንብና አሰራር መመሪያዎች ይኖረዋል።
5) የብልፅግና የሴቶች ሊግ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲው አደረጃጀት ትይዩ መዋቅሮች ይኖሩታል።
6) በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲ የአመራር አደረጃጀት በትይዩ ለሚገኘው የብልፅግና የሴቶች ሊግ አደረጃጀት የቅርብ አመራርና ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል።
7) ከፓርቲው ስራ አስፈፃሚ ውጭ ባሉ በየደረጃው የሚገኙ የብልፅግና የሴቶች ሊግ የአመራር አደረጃጀቶች ኃላፊና ምክትል ኃላፊ በትይዩ በሚገኙ የፓርቲው የአመራር አደረጃጀቶች ስብሰባዎች ያለ ድምፅ ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ።

## አንቀፅ ሰላሳ - የብልፅግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ

1) የብልፅግና ወጣቶች ሊግ ዋነኛ ተልእኮ የኢትዮጵያና የህዝቦቿን ሁለንተናዊ ብልፅግና ለማረጋገጥ ወጣቶች የሚጠበቅባቸውን ወሳኝ ሚና እንዲወጡ ለማስቻል እና የወጣቶችን ታሳትፎና ተጠቃሚነትና ለማረጋገጥ የማስተባበርና የመሪነት ሚና መጫወት ነው።
2) የወጣቶችን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ታሳትፎና ተጠቃሚነት ለማጎልበት የወጣቶች የመታገያ መድረክና ድምፅ ሆኖ ያገለግላል።
3) ዕድሜው ከ14- 35 ዓመት የሆኑ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የብልፅግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ አባል መሆን ይችላል። ዝርዝር አፈፃፀሙ የብልፅግና ፓርቲ የወጣቶች ሊግ በሚያወጣው መስፈርትና የአሰራር መመሪያ ይወሰናል።
4) ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ የሊጉ አባል የፓርቲው አባል መሆን አለበት።
5) የብልፅግና የወጣቶች ሊግ ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና የአሰራር መመሪያዎች በማይቃረን ሁኔታ የራሱ መተዳደሪያ ደንብና አሰራር መመሪያዎች ይኖረዋል፤

6) የብልፅግና ወጣቶች ሊግ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲው አደረጃጀት ትይዩ መዋቅሮች ይኖሩታል።
7) በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲ የአመራር አደረጃጀት በትይዩ ለሚገኘው የብልፅግና የወጣቶች ሊግ አደረጃጀት የቅርብ አመራርና ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል።
8) ከፓርቲው ስራ አስፈፃሚ ውጭ ባሉ በየደረጃው የሚገኙ የአመራር አደረጃጀቶች ኃላፊና ምክትል ኃላፊ በትይዩ በሚገኙ የፓርቲው የአመራር አደረጃጀቶች ስብሰባዎች ያለ ድምፅ ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ።
9) የፓርቲው ሙሉ አባል ያልሆነ የብልፅግና የወጣቶች ሊግ አባል በምርጫ በሚያዙ የፓርቲው የስራ ቦታዎች መወዳደር አይችልም፤ በልዩ ሁኔታ ካልተጋበዘ በስተቀር በፓርቲው የአባላት ወይም የአመራር ስብሰባዎች መሳተፍ አይችልም።

# ምዕራፍ አምስት

## V. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀፅ ሰላሳ አንድ - የስልጣን ዘመን

1) የፓርቲው ፕሬዝዳንት፣ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንቶች የኃላፊነት ዘመን ጣራ 10 ዓመት ይሆናል፣ የሌሎች አመራሮች የኃላፊነት ዘመን ማዕከላዊ ኮሚቴው በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል።
2) የአመራሮች የእድሜ ጣሪያ 65 ዓመት ይሆናል።

### አንቀፅ ሰላሳ ሁለት - የፓርቲው የፋይናንስ ምንጮች

የፓርቲው የፋይናንስ ምንጮች ከአባላት መዋጮ፣ በሀገሪቱ ሕግ መሰረት ከፓርቲው ደጋፊዎች እና ወዳጆች ከሚገኝ ድጋፍ ይሆናል።

### አንቀፅ ሰላሳ ሶስት - የፓርቲው የሰው ሀብት፣ ንብረት፣ ፋይናንስና የሂሳብ መዛግብት የአሰራር ስርዓት

1) የፓርቲው የሰው ሀብት፣ ፋይናንስና ንብረት ማዕከላዊ ኮሚቴ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚተዳደር ይሆናል፤

2) ፓርቲው የተሟሉና ትክክለኛ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣ በውስጥና በውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ያስመረምራል፤

3) በፓርቲው ገንዘብና ንብረት ላይ የመወሰን ስልጣን ማዕከላዊ ኮሚቴው ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## አንቀፅ ሰላሳ አራት - በፓርቲው ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች አፈታት ስርዓት

1) በፓርቲው አካላት ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች በዚህ ደንብ ውስጥ በተደነገጉ የአሰራር ስርዓቶች መፈታት አለባቸው፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት መፈታት ካልቻለ በሀገሪቱ የምርጫ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ-ምግባር ሕግና በሌሎች ሕጎች መሰረት ይፈታል፤

## አንቀፅ ሰላሳ አምስት - የፓርቲው ውህደት፤ ቅንጅት፤ ወይም ግንባር የመፍጠር ስርዓት

1) ፓርቲው ከሌሎች ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ጋር ውህደት ወይም ቅንጅት ወይም ግንባር መፍጠር ይችላል፤

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው ተፈፃሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ የምርጫ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ-ምግባር ዐዋጅ መሰረት መሆኑን ማእከላዊ ኮሚቴ ያረጋግጣል፤

3) ማዕከላዊ ኮሚቴው በኢትዮጲያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ስነ-ምግባር ዐዋጅ መሰረት መሆኑን ካረጋገጠና የውህደት ወይም የቅንጅት ወይም ግንባር የመፍጠር የውሳኔ ሐሳቡን ከተቀበለው በኋላ ለፓርቲው ጉባኤ አቅርቦ ያፀድቃል፤

## አንቀፅ ሰላሳ ስድስት - የፓርቲው መፍረስ

የፓርቲው ጉባኤ ቢያንስ በሶስት አራተኛ (3/4) ድምፅ ፓርቲው እንዲፈርስ ሊወስን ይችላል።

## አንቀፅ ሰላሳ ሰባት - የፓርቲው አማካሪ የመማክርት ጉባኤ

1) ፓርቲው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎቹን ለማሳካት የተለያዩ ሙያ ያላቸውን ምሁራንና ታዋቂ ግለሰቦችን ያቀፈ የፓርቲው የመማክርት ጉባኤ በፕሬዝዳንቱ አቅራቢነት በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፤

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በክልል የፓርቲ ፅ/ቤት ኃላፊ አቅራቢነት የክልል አመራር ኮሚቴዎች የመማክርት ጉባኤ ሊያቋቁሙ ይችላል፤

## አንቀፅ ሰላሳ ስምንት - የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ የበላይነት፣

1) መተዳደሪያ ደንቡ የፓርቲው የበላይ ሕግ ስለሆነ በፓርቲው አካላትና አባላት ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል፤
2) በመተዳዳሪያ ደንቡና በሌሎች የፓርቲ ሰነዶች መካከል ግጭት ሲያጋጥም የዚህ መተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች የበላይነት ይኖራቸዋል፤

## አንቀፅ ሰላሳ ዘጠኝ - መመሪያ የማውጣት ስልጣን

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ለተለያዩ አካላት የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ይህን ደንብ ስራ ላይ ለማዋል የሚያግዙ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

## አንቀፅ አርባ - መተዳደሪያ ደንቡን ስለማሻሻል፣ መቀየር እና ስለመሻር

1) ይህን መተዳደሪያ ደንብ ሊያሻሽል፣ ሊቀይርና ሊሽር የሚችለው የፓርቲው ጉባኤ ብቻ ነው፣
2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመተዳደሪያ ደንቡ የማሻሻያ ሐሳብ ሊቀርብ የሚችለው፤

   ሀ/ በፕሬዝዳንቱ ወይም፣

   ለ/ በማዕከላዊ ኮሚቴው $^{1}/_{3}$ ድምፅ ድጋፍ ሲያገኝ ወይም፣

   ሐ/ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አብላጫ ድምፅ ድጋፍ ሲያገኝ ወይም ፣

   መ/ በኢንስፔክሽንና ስነ-ምግባር ኮሚሽን አባላት ½ ድምፅ ድጋፍ ሲያገኝ፣

3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት የቀረበ የማሻሻያ ሐሳብ ለፓርቲው ጉባኤ መቅረብ የሚችለው በማዕከላዊ ኮሚቴው በአብላጫ ድምፅ ድጋፍ ካገኘ ነው፤
4) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ (3) መሰረት በማዕከላዊ ኮሚቴ በቀረበው የማሻሻያ ሐሳብ ላይ የፓርቲው ጉባኤ በአብላጫ ድምፅ ከወሰነ መተዳደሪያ ደንቡ ይሻሻላል።

**አንቀፅ አርባ አንድ - መተዳደሪያ ደንቡ ስለሚፀናበት ሁኔታ**

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በብልፅግና ፓርቲ 1ኛ ጉባኤ ከፀደቀበት ________________ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**የካቲት 2014 ዓ.ም**
**ብልፅግና ፓርቲ (ብልፅግና)**
**አዲስ አበባ**